# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት





## የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋትና አቅም ለመገንባት የሚሰጠውን ድጋፍ እና ክትትል በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲትሪፖርት



ነሐሴ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

1.1 መግቢያ ........ 1

የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አመሰራረት ........ 1

የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር ........ 2

የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ........ 2

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ........ 2

የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር ........ 2

የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ........ 4

ድርጅታዊ መዋቅር ........ 4

የሰው ኃይል ........ 4

የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 5

1.2 የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለኢንዱስትሪው የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት መግለጫ ........ 6

ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ........ 7

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት ........ 7

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 7

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት ........ 8

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 8

የኦዲቱ ወሰን ........ 8

የኦዲቱ ዘዴ ........ 8

ክፍል ሁለት ........ 10

የኦዲት ግኝቶች ........ 10

2.1 ኢንስቲትዩቱ፣ ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል፣ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን እንዲሁም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ለማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 10

ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ወቅታዊ መረጃ እና የፕሮጀክት ፕሮፋይል ስለማዘጋጀቱ ........ 10

ኢንስቲትዩቱ ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠውን ድጋፍና ክትትል በተመለከተ ..... 12

የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሃ ግብሮችን በተመለከተ፣..... 14

ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ጥናቶችን በተመለከተ..... 17

የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅም መገንባትን በተመለከተ፣..... 18

ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ ከመንግስት እና ከግል ተቋማት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ..... 20

2.2 የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማምረት እንዲችሉ እና ምርቶቹም የገበያ ድርሻን ማሳደግ እንዲችሉ በኢንስቲትዩቱ የሚሰጠው ድጋፍ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤..... 21

በኢንስቲትዩቱ ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጡ የቴክኒክ ድጋፎችን በተመለከተ ..... 21

ብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥ እና በውጭ አገር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ፣..... 23

የውድቅዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና አያያዝን በተመለከተ ..... 25

ክፍል ሶስት ..... 27

መደምደሚያ ..... 27

ክፍል አራት ..... 30

የማሻሻያ ሃሳቦች ..... 30

አባሪ 1 የኢንስቲትዩቱ ሥዕላዊ የአሰራር ስርዓት መግለጫ (System description)..... 35

***አባሪ 2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች*** ..... 36

አባሪ 3 በናሙና የታዩ ኢንዱስትሪዎች ዝርዝር ..... 39

አባሪ 4 የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ድርጅታዊ መዋቅር ..... 40

አባሪ 5፡ የብረታ ብረት ዘርፍ ኢንስቲትዩቱ በጥናት የለያቸው ተግዳሮቶች ..... 41

# ክፍል አንድ

## 1.1 መግቢያ

**<u>የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አመሰራረት</u>**

1. የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚመደብ ሲሆን የመሰረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ በመሰረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ የሚመደቡት ብረትን ከማጣራት ጀምሮ የተለያዩ መጠን ያላቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ምርቶችንና እነዚህን ምርቶች በግብዓትነት በመጠቀም ዝርግ፣ ጥቅልልና ልሙጥ ብረቶችን፣ የተለያዩ ቅርፅ ያላቸውን ድፍንና ክፍት ረጃጅም የብረት ምርቶችን፣ ሽቦዎችን፣ የሽቦ ገመዶችን፣ ቆርቆሮዎችንና ምስማሮችን የማቅለጥ፣ የማሞቅና የመዳጥ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚመረቱ ናቸው፡፡

2. በኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ የሚመደቡት ደግሞ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ውጤትን በግብዓትነት በመጠቀም የተለያዩ ቅርፅ ማውጫ ቴክኖሎጂዎችን ማለትም በማቅለጥ ቅርፅ ማውጣት፣ በማነጥ፣ በብየዳና በመቀጥቀጥ መሳሪያዎችንና የተለያዩ መገልገያ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ናቸው፡፡

3. በአገራችን የብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ንዑስ ዘርፍ በኢትዮጵያ መንግስትና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም መካከል በ1973 ዓ.ም የተደረገው የዕርዳታ ስምምነት ለዘርፉ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት መፈጠር መነሻ ነበር፡፡

4. በ1975 ዓ.ም የኢንጂነሪንግ ዲዛይንና ቱል ድርጅት በመባል የተመሰረተ ሲሆን ዓላማውም መሳሪያዎችን፣ ቱሎችና ሌሎች ቁሳዊ ግኝቶችን ዲዛይን በማድረግና በመፈብረክ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ ማድረግ ነበር፡፡

5. ከኢንጂነሪንግ ዲዛይንና ቱል ድርጅት ጋር ተመሳሳይ ተግባር ሲያከናውኑ ከነበሩ ሌሎች ተቋማት ጋር በመዋሀድ የመሰረታዊ ብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 47/1989 ተመሰረተ፡፡ የኤጀንሲው ተግባርም የምርት ልማትና የኢንዱስትሪ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት ነበር፡፡ ሆኖም በሐምሌ1996 ዓ.ም የብረታ ብረት ምርት ልማት ማዕከል በሚል ስያሜ እንዲቀየር ተደረገ፡፡ ዓላማውም በገበያ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ አዳዲስ የምርት ልማት ስራዎችን ማከናወንና ለጥቃቅንና አነስተኛ

ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ለገጠር ልማት ተስማሚ ቴክኖሎጅዎች፣ የዲዛይንና ማኑፋክቸሪንግ አቅም ማጎልበት ነበር፡፡

6. የብረታ ብረት ምርት ልማት ማዕከል በቀድሞው በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ስር እስከ ግንቦት 2002 ዓ.ም ሲንቀሳቀስ ቆይቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/2002 ለአሁኑ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ቦታውን አስረከበ፡፡ የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የአገሪቷን የብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት ሲሆን ተጠሪነቱም ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡

# የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር

## የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ

7. የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ አቅምን ለማሳደግ የሚያስችል ምርምርና ጥናትን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ የኢንቨስትመንት፣ የግብይትና የማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ድጋፍ ለልማታዊ ባለሀብቱ በመስጠት ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማድረግ ነው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ራዕይ

8. የላቀ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ልማትና የኢንጂነሪንግ አቅምን የሚያሳድግ ብቁ ተቋም በመሆን የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ፈጣንና ቀጣይ ዕድገት ያለውና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ በመሆን በ2015 ዓ.ም. የዜጎችን የነፍስ ወከፍ የብረት ድርሻ መካከለኛ ዕድገት ካላቸው አገሮች ተርታ ማድረስ ነው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ዓላማ

9. የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የአገሪቷን የብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግርን በማፋጠን ኢንዱስትሪዎቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ፈጣን ልማት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት ነው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር

10. ኢንስቲትዩቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/2002 መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፣

ለ. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ ለዘርፉ የመረጃ ማዕከል ማስተላለፍና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

ሐ. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪነግ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ ወደየዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች የአዋጭነት ጥናት ማድረግ፣ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትል ማድረግ እና በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ መስጠት፣

መ. በብረታ ብረት እና በኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፣

ሠ. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪነግ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ልማት የሚያግዙና ዘርፉን ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፣ ለሠልጣኞችም የምስክር ወረቀት መስጠት፣

ረ. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማከናወን፣

ሰ. በምርት ሂደት፣ በምርት እቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣

ሸ. ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፣

ቀ. የብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን መደገፍ፣

በ. ለብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፣

ተ. የግብአትና የምርት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ መስጠት፣

ቸ. የውዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና ግብይት ስርዓት የሚይዝበትን ሁኔታ ማጥናትና ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን መከታተል፣ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውና አዋጭነታቸው የተረጋገጠላቸውን የብረትና ተዛማጅ ማዕድናትን የማቅለጥና የማጣራት ስራዎችን መደገፍ፣

ኀ. ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና የምርት ልማት ሥራ ማከናወን፣

ነ. ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር ያግዛል፣

ኘ. ለብረታ ብረት እና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርቶች የገበያ ጥናቶችን ማከናወን፣

አ. ለተጠቃሚዎች የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል መስጠት፣

ከ. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአግባቡ ክፍያ መጠየቅ፣

ኸ. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣

ወ. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ማከናወን

የሚሉ ናቸው

# የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

## ድርጅታዊ መዋቅር

11.ኢንስቲትዩቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተር የሆኑ 8 ዳይሬክቶሬቶች እና አንድ ጽ/ቤት አሉት፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 4 ተያይዟል፡፡

## የሰው ኃይል

12.ኢንስቲትዩቱ እስከ ሰኔ 2006 ዓ.ም ድረስ 161 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 63ቱ (39%) ሴቶች ሲሆኑ 98ቱ (61%) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል

በትምህርት ደረጃ ሲታይ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 13 (8%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 67(42%)፣ ኮሌጅ(አድቫንስ) ዲፕሎማ 8(5%)፣ ቴክኒክና ሙያ ዲፕሎማ 38 (23%) እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃና ከዚያ በታች ያሉ ሰራተኞች 35 (22%) ናቸው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ

13. የብረታ ብረትና ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ስራውን የሚያከናውነው ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን ከ2003-2006 የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጭ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2003 | 7,432,379 | 6,850,815 | (92%) |
| 2004 | 11,553,644 | 11,100,315 | (94%) |
| 2005 | 14,066,881 | 13,108,550 | (93%) |
| 2006 | 42,011,870 | 11,711,059.18 (9 ወር) | 27.88% (9 ወር) |

## 1.2 የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለኢንዱስትሪው የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል ተግባር የአሰራር ስርዓት መግለጫ

14. ኢንስቲትዩቱ ለተጠቃሚ አካላት መረጃ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ የፕሮጀክት ፕሮፋይል ጥናት ማዘጋጀት፣ የአዋጭነት ጥናት ማዘጋጀት፣ በፕሮጀክት ሂደት ላይ ያሉ ኢንቨስትመንቶችን መደገፍና መከታተል፣ የቴክኖሎጂ መረጣ ድጋፍ መስጠት፣ የዲዛይንና ግንባታ ፕላን ድጋፍ ማድረግ፣ የኮሚሽኒንግ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣ አለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ምርት እንዲያመርቱ የምርት ደረጃ እንዲወጣ መደገፍ፣ ዓለም አቀፍ የሥራ አመራርና የጥራት ሥርዓቶችን በኢንዱስትሪዎች መዘርጋት፣ በኢ- አበላሽ ፍተሻ (Non-Destructive Testing) መሳሪያዎች የምርት ጥራት ፍተሻ አገልግሎት መስጠት፣ የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንዲተገበሩ ማድረግ፣ የብረታብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የሰው ኃይል አቅም በቀጣይነት በሥልጠና መገንባት፣ በሀገር ውስጥ ሊለሙ የሚችሉ የተለዩ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ የምርት ዲዛይንና የማኑፋክቸሪንግ አቅም ማሳደግ፣ የለሙ ምርቶችን ወደ ኢንዱስትሪው እንዲሸጋገሩ ማድረግ፣ ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው በተለይም ኤክስፖርት ምርቶችን ለሚያመርቱ እንዱስትሪዎች የቴክኒክ ድጋፎችን መስጠት፣ በውጭ አማካሪዎች የሚከናወኑ የምርት ልማት ሥራዎችን መለየትና የተለዩትንም መገምገምና በመዋዋል ማሸጋገር፣ የምርምር፣ የፖሊሲና የስትራቴጂ ሀሳቦችን ማመንጨትና እንዲተገበሩ ማድረግ፣ የገቢ ምርቶችን መለየትና በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ፣ ዘመናዊ የግብይት የሥራ አመራር ሥርዓት መፍጠር፣ የንዑስ ዘርፉን ምርት ማስተዋወቅ፣ የግብአትና የምርት ትስስር ድጋፍ መስጠት፣ ለንዑስ ዘርፉ ምርቶች የውጭ ገበያ ማፈላለግ፣ የአገር ውስጥ አምራቾችን የሚያበረታታ ግብይት ሥርዓት መዘርጋት፣ የአገር ውስጥ የውዳቂ ብረታ ብረትና አገልግሎታቸውን የጨረሱ ከብረታ ብረት የተሰሩ ዕቃዎችና መሳሪያዎች ማስወገጃ የአሰራር ሥርዓትና መመሪያ ማዘጋጀት ናቸው፡፡ ስእላዊ መግላጫው በአባሪ 1 ተያይዞል፡፡

### የኦዲቱ ዓላማ

15.የኦዲቱ ዓላማ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን አቅም ለመገንባት የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን፣ ኢንስቲትዩቱ እና ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መስራታቸውን፣ ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ

*መደረጉን ለማረጋገጥ ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡*

## ***ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ***

16. *ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋትና አቅም ለመገንባት የሚሰጠው ድጋፍ እና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡*

## ***የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት***

## ***የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች***

17. *ከላይ የተገለፀውን የኦዲት አላማ ለማሳካት ሁለት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች* (Audit issues) *የተለዩ ሲሆን በሁለቱም የትኩረት አቅጣጫዎች ሥር ሁለት ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡*

1. *ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣*

    1.1 *ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን በፕሮጀክት እና ምርት ማምረት ሂደት ላይ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣*

    1.2 *ኢንስቲትዩቱ፣ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ እና ለመደገፍ በቅንጅት የሚሰራበት አሰራር መኖሩን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤*

2. *ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማምረት እንዲችሉ እና ምርቶቹም የገበያ ድርሻን እንዲያሳድጉ ለማስቻል በኢንስቲትዩቱ የሚሰጠው ድጋፍ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤*

2.1 ኢንስቲትዩቱ፣ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ለማጎልበት፣ የምርት ጥራት እና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ትኩረት የተሰጣቸውን መካከለኛና ከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የገቢ ምርቶችን መተካት የሚችሉ ተወዳዳሪ ምርቶች በዓይነት፣ በጥራት እና በመጠን ማምረት የሚያስችል አቅም የተፈጠረ መሆኑን መገምገም፤

2.2 ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የገበያ ድርሻ ማስፋፋት የሚችል ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

18. ከላይ የተለዩትን የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 29 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተው ኢንስቲትዩቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተቋቋመበት ደንብ፣ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ የኢንስቲትዩቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የተለያዩ መመሪያዎች፣ በኢንስቲትዩቱ የተጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሰነድ፣ ውጤት ተኮር የምዘና ሰነድ እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

### የኦዲቱ ወሰን

19. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2003-2006 3ኛ ሩብ ዓመት ድረስ ያሉትን በጀት ዓመታት የሥራ ክንውኖች ነው፡፡

### የኦዲቱ ዘዴ

20. ኦዲቱ የተከናወነው በብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተዘረጋው

የአሰራር ስርዓት አፈፃፀምና ውጤታማነትን የሚመለከቱ የተለያዩ ሠነዶችና ማስረጃዎችን በመከለስ፣ ኢንስቲትዩቱ በቅርበት ከሚከታተላቸው 60 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ  በናሙና የተመረጡትን 8 በብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን በአካል በማየት፣ የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ እንዲሁም ከዘርፉ ጋር በጋራ ለሚሰሩ 4 መ/ቤቶች ቃለ መጠይቆችን በማቅረብና ማስረጃዎችን በመከለስና መበሰብሰብ እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ የሚገኙ የዳይሬክቶሬት ኃላፊዎችን ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ፣ የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ከሆኑት ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ እንዲሁም  በናሙና የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### 2.1 ኢንስቲትዩቱ፤ ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል፣ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን እንዲሁም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ለማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

<u>ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ወቅታዊ መረጃ እና የፕሮጀክት ፕሮፋይል ስለማዘጋጀቱ</u>

21. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የሚገልጽ ዝርዝር ወቅታዊ መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የኢንዱስትሪዎችን ፕሮፋይል ሊያዘጋጅ፣ የዋና ዋና ግብዓቶች የዋጋ ተመን መግለጫ (factor cost sheet) ሊያደራጅና ሊያሰራጭ እንዲሁም ለዘርፉ ስለሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ለህብረተሰቡ ሊያስተዋውቅና የሰበሰባቸውን መረጃዎች ለባለሀብቶች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

22. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ኢንስቲትዩቱ ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተላቸው 52 ኢንዱስትሪዎች ለሁሉም የካምፓኒ ፕሮፋይል ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤ በኢንስቲትዩቱ የተያዘው የኢንዱስትሪዎችን ዝርዝር መረጃው ያልተሟላ መሆኑ ማለትም (የድርጅቱን አላማ፣ የካፒታል መጠን፣ ወደ ሥራ የገባበት ዘመን፣ የተጠቀማቸው ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች አይነት፣ ለአገር የፈጠረው ፋይዳ ማለትም በስራ እድል፣ በአመት የማምረት አቅም፣ የተጠቀመው ቴክኖሎጂ፣ የሚጠቀመው ግብአትና መጠን ወዘተ) መሆኑ፤ የዋና ዋና ግብዓቶች የዋጋ ተመን መግለጫ የተዘጋጀ ቢሆንም ማስረጃው ለሚጠይቁ ብቻ የሚሰጥ እንጂ መረጃውን የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ማግኘት የሚችልበትን ዘዴ በመጠቀም ለምሳሌ በመረጃ ድረገፅ (web-site) ያልተቀመጠ መሆኑ እና ኢንስቲትዩቱ ስለሚሰጣቸው ድጋፎች ለህብረተሰቡ በሚገባ ያላስተዋወቀ መሆኑ ታውቋል፡፡

23. ይህን በተመለከተ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ መረጃዎችን በዳታ ቤዝ ለመያዝ የሞከሩ ሲሆን ወደፊት እንደሚያጠናክሩት፣ ኢንስቲትዩቱን በማስተዋወቅ አንዳንድ የምክክር መድረኮች ማዘጋጀታቸውን ገልፀዋል፡፡

24. ስለ ጉዳዩ በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ ላይ የኢንስቲትዩቱ ኃላፊ በሰጡት አስተያየት በሥራ ላይ ያሉ ድርጅቶች ፕሮፋይል በተደራጀ ሁኔታ ያልተያዘ ስለሆነ ይህን እንደግብዓት የሚወስዱት መሆኑን፣ ከመውጫ ስብሰባው በኋላም መረጃዎችን በድረ ገፅ የሚያስቀምጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

25. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የሚገልፅ የተሟላ ወቅታዊ መረጃ በዳታ ቤዝ ባለመያዙ በአገራችን በብረታ ብረት ዘርፍ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን በግልፅ ለማሳየት የማያስችል ከመሆኑም በላይ፣ ኢንስቲትዩቱ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እና ድጋፎች በስፋት ባለማሳወቁ በዘርፉ ሊሰማሩ የሚፈልጉና የሚችሉ ባለሀብቶች ከኢንስቲትዩቱ ድጋፍ ሊያገኙ የሚችሉ ስለመሆኑ ግንዛቤ እንዳይፈጠር ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>**ኢንስቲትዩቱ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡ ባለሀብቶች የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ማድረጉንና የተሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን መከታተሉን በተመለከተ፤**</u>

26. ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡ ባለሀብቶች የመሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች (ውሃ፣ ኤሌክትሪክ፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ) እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

27. ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የመሰረተ ልማት አገልግሎት ድጋፍ እንዲያገኙ የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ የሚረዳቸው ቢሆንም ድጋፉን ስለማግኘታቸው ክትትል የማያደርግ መሆኑን፣ እንዲሁም የባንክ ብድር አቅርቦት፣ የስልክ፣ የመብራት መቆራረጥ ችግሮች እስካሁን ያልተፈቱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ የቀረበላቸው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች ገልፀዋል፡፡

28. እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማለትም በየፕሮጀክት ሂደት (project phase) የሚያስገቡዋቸውን የተለያየ መጠን ያላቸው ለግብዓትነት የሚውሉ ቁሳቁሶችና ማሽነሪዎች ወዘተ ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን የማይከታተል መሆኑ ታውቋል፡፡

29. ስለ ጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የኢንጂነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት መልስ በኢንቨስትመንት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን የቅርብ ክትትል የሚያደርጉ ሲሆን ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎችን ብቻ በመለየት የማይከታተሉ መሆኑን፣ ሆኖም የሙከራ ምርት እስከ ሙሉ አቅም ምርት ለማምረት መለዋወጫዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲገባላቸው በሚመለከተው አካል አስተያየታቸውን ሲጠየቁ የሚሰጡ መሆኑን እና በዛው መሰረት አገልግሎት ላይ መዋላቸውን የሚከታተሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት ዳይሬክተሩ ድጋፍ ማግኘታቸውን የሚከታተሉ ሲሆን ችግሮቹ ወዲያው ላይፈቱ እና ብዙ ውጣ ውረድ ስለሚኖራቸው ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ የምንሰጠው ድጋፍም ሆነ የምንፅፈው የድጋፍ ደብዳቤ ወዲያው መልስ ላይገኝለት ስለሚችል ነው ብለዋል፡፡

30. የኢንስቲትዩቱ የኢንጂነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ይህን ይበሉ እንጂ ለኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ግብአቶችና ማሽነሪዎችን በተመለከተ ክትትል የማያደርጉ እና በቀረበው ማስረጃ ውስጥም የተገኘው ፕሮጀክቶችን የመከታተልና የማማከር ስራ ቢሰሩም ስለኢንቨስትመንት ማበረታቻ ክትትል የሚደረግበት ስርዓትም ሆነ ቼክ ሊስት ያልተዘጋጀለት መሆኑ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ የቀረበላቸው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች በመሰረተ ልማት፣ በመብራት፣ በጉምሩክና እና በመሳሰሉት ችግሮቻቸው ያልተፈታላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

31. በዘርፉ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡ ባለሀብቶች የመሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ድጋፍና ክትትል ውጤታማ ባለመሆኑ ባለሃብቶቹ ለተጨማሪ ወጪ እና ያለአግባብ ጊዜ የሚያባክኑ መሆኑ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ስም የሚገቡ ማናቸውም ግብአቶችና ማሽነሪዎች ለታለመላቸው አላማ እና በወቅቱ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የማይታወቅ ከመሆኑም በላይ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍትና ፍትሃዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>ኢንስቲትዩቱ ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠውን ድጋፍና ክትትል በተመለከተ</u>

32. ኢንስትትዩቱ ወደ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሚገቡ ባለሃብቶች የፕሮጀክት ፕሮፋይል፣ የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ እንዲሁም በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በመሳሪያዎች ተከላ፣ በርክክብ ፍተሻ እና በማማከር ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ከ2004-2007 ዓ.ም በስትራቴጂክ እቅዱ ላይ የአዋጭነት ጥናት በማጥናት ለባለሃብቶች እንደሚያሰራጭ ቢገልፅም ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በ2004 በጀት ዓመት በኢንስቲትዩቱ ከተለዩት 103 አማራጭ የኢንቨስትመንት እድሎች የተሟላ የፕሮጀክት ፕሮፋይል በማጠናቀቅ ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው 20 አማራጭ የኢንቨስትመንት እድሎች የቅድመ አዋጭነት ጥናት ለማከናወን የታቀደ ቢሆንም ሥራውን በታቀደው መሰረት ሙሉ በሙሉ ለማከናወን ያልተቻለ መሆኑ፣ 10 ለሚደርሱ ፕሮጀክቶች ድጋፍ ለመስጠት አቅዶ ለ5 ብቻ (50 በመቶ) ያከናወነ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ በ2006 በጀት ዓመት 7 ለሚደርሱ ፕሮጀክቶች የዲዛይንና ግንባታ፣ የኮሚሽኒንግ፣ የማሽነሪ ተከላና የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ቢያቅድም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት እስከ 3ኛ ሩብ ዓመት 30 ለሚሆኑ የምርት ዓይነቶች የቅድመ አዋጭነት ጥናት (ፕሮጀክት ፕሮፋይል) ለመስራት አቅዶ 14 (የዕቅዱ 46 በመቶ) የቅድመ አዋጭነት ጥናቶች ብቻ ያዘጋጀ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የኢንጂነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቅድመ አዋጭነት ጥናትና የፕሮጀክት ፕሮፋይል አንድ አይነት ይዘት ያላቸው በመሆኑ እንደ አንድ ቃል (interchangeblly) የሚጠቀሙበት መሆኑን፣ የአዋጭነት ጥናት ብዙ ጊዜና የሰው ሃይል የሚፈልግ በመሆኑ በእቅዱ መሰረት ያልተከናወነ ሲሆን ባለሃብቶች የአዋጭነት ጥናት አጥንተው ሲያመጡ የማበልፀግ ስራዎችን እንደሚሰሩ፣ በፕሮጀክቶች የዲዛይንና ግንባታ፣ የኮሚሽኒንግ፣ የማሽነሪ ተከላና የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ክትትል ለማድረግ በእቅዱ መሰረት እንዳይከናወን የሰው ሃይል እውቀትና ክህሎት ክፍተት በመኖሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ኢንስቲትዩቱ ለባለሃብቱ የአዋጭነት ጥናት እያዘጋጀ ሊያቀርብ የማይችል እና የማይገባ በመሆኑ በእቅድ መያዙ ያልተገባ እንደነበረ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልፀዋል፡፡

35. የኢንጂነሪንግ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ይህን ይበሉ እንጂ ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጀው 2004-2007 ስትራቴጂክ እቅድ እና በአመታዊ እቅዶች ላይ የአዋጭነት ጥናት፣

በተናጠል የፕሮጀክት ፕሮፋይል እና የቅድመ አዋጭነት ጥናት ያቀዱ በመሆኑ ሁለቱ (የፕሮጀክት ፕሮፋይልና የአዋጭነት ጥናት) ተመሳሳይ ትርጓሜ አላቸው የሚለውን ለመቀበል የሚያስቸግር ሲሆን የማበልፀግ ስራ ስለመስራቱ የሚያሳይ ቼክ ሊስት ወይንም የተሰራውን ስራ የሚገልፅ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ለባንክና ለሚመለከታቸው አካላት በፃፋዋቸውን ደብዳቤዎችን እንደማበልፀግ ስራ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

36. ኢንስቲትዩቱ በስትራቴጂክ እቅድ የሚያካትታቸውን ዕቅዶች ግልፅ፣ ሊለኩ የሚችሉ እና ወደተግባር ሊቀየሩ የሚችሉ ሊሆኑ ሲገባ ይህ ባለመሆኑ አፈፃፀሙን ለመገምገም ካለማስቻሉም በላይ እና የሚሻሻሉ ሃሳቦችን ለመስጠት የሚያስቸግር ሆኗል፡፡

## <u>የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሃ ግብሮችን በተመለከተ፣</u>

37. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የኢንዱስትሪዎችን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሊያስጸድቅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዘርፉ ላይ የተሰማሩና ሊሰማሩ የሚፈልጉ ባለሃብቶች በሥራቸው ላይ በአንድም ሆነ በሌላ መልክ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን፣ ደንቦችን እና የተለያዩ የአሰራር መመሪያዎችን በማጥናትና በመለየት ለሚመለከተው አካል የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ ችግሮቹ የሚቀረፉበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል፡፡

38. ኢንስቲትዩቱ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የፖሊሲና የህግ ድጋፍ፣ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ የግብይት ስትራቴጂ ለመንደፍ እና ተጓዳኝ ድጋፍ ለማድረግ ከ2004-2007 በስትራቴጅክ እቅድ ቢይዝም በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ ያልገለፀ እና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

39. በኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚያግዙ አዳዲስ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲወጡና የአሰራር ሥርዓቶች እንዲዘረጉ የቀረበ ጥናት ባይኖርም ለዘርፉ ችግር የፈጠሩ ነባር ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተለይተው እንዲሻሻሉ በግንቦት ወር 2006 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በጋራ ተጠንቶ መቅረቡ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በጥናቱ ከተለዩት መካከል፣-

- መንግስት በሚያከናውናቸው የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ዘርፈ ብዙ ግብአቶችን (የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችን፣ የጭነትና ገልባጭ ተሸከርካሪዎችን፣ የመስክ ተሸከርካሪዎችን፣ አርማታ ብረቶችን፣ ቆርቆሮዎችን፣ ቱቦላሬዎችን፣ ትራንስፎርመር፣ የኤሌክትሪክ ሞተሮችና ገመዶች ወዘተ) የሚገዛ ሲሆን በስራ ላይ ያለው የመንግስት የጨረታ መመሪያ የአገር ውስጥ አምራቾች እንዲጠቀሙ ቅድሚያ የሚሰጥ ወይም ከጨረታው የተወሰነ ድርሻ መጠን ለአገር ውስጥ አምራቾች የሚሰጥ ባለመሆኑ፣ የሚወጡ ጨረታዎች በማደግ ላይ ያለውን የሀገር ውስጥ አምራች አቅም ያላገናዘቡ መሆናቸው፣ ለምሳሌ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው ግዥ በአጭር የማስረከቢያ ጊዜና የጥቅል አቅርቦት በማስቀመጥ የሀገር ውስጥ አምራች የማግለል ሂደት የሚታይ መሆኑ፣
- ለግብርና ግብዓቶች የተሰጠው የቀረጥ ማበረታቻ /መብት/ በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽንም ሆነ በሌሎች አምራች ድርጅቶች ለሚመረቱ ትራክተሮች፣ ተቀፅላዎችና የውሃ ፓምፖች የማያካትታቸው መሆኑ፣
- ከኢንቨስትመንት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መለዋወጫዎች በሚያስገቡ ጊዜ የማሽኑን ወይም የተሽከርካሪውን ዋጋ 15 በመቶ ከቀረጥ ነፃ መለዋወጫ የሚፈቀድ ሲሆን በአገር ውስጥ ለተመረቱ የካፒታል እቃዎች መለዋወጫ የ15 በመቶ የቀረጥ ነፃ መብት ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- በዋራንቲ ጊዜ ለተበላሹ ወይም ቀድመው ተሟልተው ባልተላኩ ግብአቶች በምትክነት ለሚገቡ እቃዎች ጉምሩክ እንደግብአት በሁለተኛ መደብ ታሪፍ ሳይሆን እንደ መለዋወጫ እቃ ከፍተኛ ቀረጥ የሚያስከፍል ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ኤል ሲ ተከፍቶ ያልገባ ነው በማለት በቅጣት የዕቃውን ዋጋ ሶስት እጥፍ እንዲከፍሉ የሚያስገድድ መሆኑ፣
- ከቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ያላቸው ባለሃብቶችና ፕሮጀክቶች የሚፈልጉትን እቃ ከሃገር ውስጥ አምራቾች ሲገዙ ከቀረጥና ታክስ ነፃ መብታቸውን ከአገር ውስጥ አምራች የማይጠቀሙ በመሆኑ ቀረጥና ታክስ ጭምር ከፍለው ለማስመለስ በሚወስደው የጊዜ ሂደት ከአገር ውስጥ አምራች ይልቅ ከውጭ እንዲገዙ የሚያበረታታ መሆኑ፣
- በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ላይ ተሰማርተው የገቢ ግብር የእፎይታ ጊዜ ከተሰጣቸው አምራቾች ላይ ሙሉ በሙሉ ወላልቀው በሚገጣጠሙ ዕቃዎችና ጥሬ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ጣቢያዎች የ3 በመቶ እንዲሁም ያለቁ ምርቶች ለደንበኞች

በሚሸጡ ጊዜ ደንበኛው 2 በመቶ ዊዝሆልዲንግ ታክስ ያለአግባብ የሚሰበስቡ መሆኑ፣

- የክብደት መጠን ልዩነት በመቶኛ (tolerance limit) ባለመኖሩ ምክንያት በክብደት መጠን ልዩነት በተለያየ ምክንያት ሲከሰት ትርፍ ጭናችኋል በሚል ተጨማሪ ቀረጥና ቅጣት ክፍያ የሚጣል በመሆኑ የአምራቾች የምርት ወጪ እንዲንር ያደረገ መሆኑ፣
- በአየር መንገድ የሚመጡ ዕቃዎች ሲወርዱ ዕቃዎች ላይ የሚደርስ ጉዳት፣ ለእቃዎች ተገቢ መጠለያ ስለማይደረግላቸው በዝናብና በፀሃይ የሚደርስባቸውን ጉዳት እንዲሁም ዕቃዎቹን ለማግኘት ረዥም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ፣ ክፍያ እና የርክክብ ጊዜ ከፍተኛ ችግር የሚታይበት መሆን፣
- ለአገር ውስጥ በአነስተኛ ተቋማት ሊሰራ የሚችልን ስራ ለውጭ ባለሃብት ክፍት በማድረጉ የአገር ውስጥ ባለሃብቱን የሚያፈናቅል አካሄድ መኖሩ፣
- ከውጭ ተመርተው የሚገቡ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር አለመደረጉ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎች ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማድረሱ፣
- የኤሌክትሪክ ኃይል በበቂ ሁኔታ አለመቅረብና በየጊዜው የሚታየው የኃይል መቆራረጥ የመለዋወጫ መቃጠልና የምርት መስተጓጎል ችግር እያስከተለ መሆኑ፣ አምራቾች ከኮርፖሬሽኑ ጋር በገቡት ውለታ እና በከፈሉት መጠን የኃይል አቅርቦት የማያገኙ መሆኑ፣
- የኤሌክትሪክ ብክነትን ለመቀነስ ተብሎ የኃይል መቆጣጠሪያ መሳሪያ (Power factor corrector) ለመግጠም የኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽኑ ከሁለት ዓመት በፊት ከፋብሪካዎች ክፍያ የሰበሰበ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ እንዲሁም በዚህም ሳቢያ አምራቾች በሚባክነው ኃይል ምክንያት ለቅጣት የተዳረጉ መሆኑ፣ እና

የመሳሰሉት ችግሮች መኖራቸው በጥናቱ ላይ ተመልክቷል፡፡ ተጨማሪ በብረታ ብረት ዘርፍ ኢንስቲትዩት በጥናት የተለዩ ተግዳሮቶች በአባሪ 5 ተያዟል፡፡

40. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከዚህ ቀደም የወጡ ደንብና መመሪያዎች በአግባቡ ለመተግበር እየሰሩ መሆኑን፣ የሚሻሻሉ ደንቦችና መመሪያዎች መኖራቸውን በመለየት ችግሮቹን በዝርዝር ከላይ በተጠቀሰው ጥናት በመለየት ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በግንቦት ወር 2006 ዓ.ም ያቀረቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ ችግር ያለባቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የትኞቹ አንቀፆች ላይ ችግር እንዳለባቸው በግልፅ በጥናቱ ውስጥ ባለመካተቱ ችግሮቹ በህግ፣ ደንብና መመሪያ ምክንያት ለመከሰታቸው ለመቀበል አዳጋች ያደርገዋል፡፡

42. በኢንስቲትዩቱ የቀረበው ጥናት ችግሮቹ የተፈጠሩት በየትኞቹ ህጎች የደንቦችና የመመሪያዎች ክፍተት እንደሆነ በግልጽ በጥናቱ ተለይቶ ባለመቀመጡ ችግሮቹ በህጎች የደንቦችና የመመሪያዎች ክፍተት የተፈጠሩ መሆናቸውን ለመለየት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ለውሳኔ ሰጭ አካላትም ውሳኔ ለመስጠትና ንዑስ ዘርፉ ላይ ተጽዕኖ ፈጠሩ የተባሉት ላይ ማሻሻያ ለማድረግ አዳጋች ሊያደርገው ከመቻሉም በላይ ኢንዱስትሪዎቹ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ መሰረት የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንዳይወጡ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

## <u>ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ጥናቶችን በተመለከተ</u>

43. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪን መሰረት ለማስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ማለትም ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙና የግብርናውን ዘርፍ የሚደግፉ ማሽነሪዎችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን፣ በውጭ ምንዛሪ የሚገዙትን በመተካት የገበያ ክፍተትን የሚሞሉ፣ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ፕሮጀክቶችን በመለየት፣ በስትራቴጂክ እና አመታዊ እቅድ በመከፋፈል ጥናትና ምርምር ሊያከናውን ይገባል፡፡ የተጠኑትን ጥናቶችና ምርምሮች ውጤት ለባለሃብቱ በማስተዋወቅ ባለሀብቱ ኢንቨስት እንዲያደርግና አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙ በማግባባት የተጠናከረ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

44. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ኢንስቲትዩቱ የብረት ማዕድንን በአገራችን ለማውጣትና ለመጠቀም የሚያስችል ጥናት እያስጠና ሲሆን በኢንዱስትሪው ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግሮችና ክፍተቶችን ሊቀርፉና ሊሞሉ የሚችሉ ጥናቶችን ለማጥናትና ለማስጠናት በስትራቴጂክ እና በአመታዊ እቅዱ ለይቶ ያላሳየ መሆኑ፣ እንዲሁም የተጠኑ ጥናቶችን በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሃብቶችን በመለየት የማሳወቅ ስራዎችን በሚጠበቅበት መጠን ያላከናወነ መሆኑ፣

- የገበያ ክፍተትን በሚሞሉ እና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማፍለቅ በመንግስትና በልማታዊ ባለሀብቱ ቅንጅት ኢንቨስት እንዲደረግ ለመስራት በስትራቴጅክ እቅድ ቢይዝም የተሰራውን ስራ ያልተገለፀ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

45. ይህን በተመለከተ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር እና የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመንግስትን የልማት አቅጣጫ ታሳቢ በማድረግ የገበያ ክፍተትን የሚሞሉና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማፍለቅ የተወሰነ ጥናት የተጠና ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ጥናቶቹን መሰረት በማድረግ ኢንቨስት ያልተደረገ መሆኑን እንዲሁም በግብርና ሜካናይዜሽን ሥራዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው እንደሰሩና ለባለሀብቶችም መልካም ተሞክሮዎችን እንዳስተዋወቁ ገልፀዋል፡፡

46. በመውጫ ስብሰባ ወቅት የኢንዱስትሪውን ችግር የሚፈታ የጥሬ ብረት ማዕድን ጥናት እየተጠና በመሆኑ ወደተግባር ሲገባ የዘርፉ ችግር በሙሉ ሊቀርፍ የሚችል መሆኑ፣ በመንግስትና በግል ባለሃብቱ በቅንጅት ኢንቨስት ማድረግ የተጠቀሰው በስህተት መሆኑ ገልፀዋል፡፡

47. የኢንዱስትሪውን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ ምርምሮችናና ጥናቶችን በእስትራቴጂክና በአመታዊ ዕቅድ በዝርዝር አካቶ እና ለይቶ ባለመሄዱ ኢንስቲትዩቱ ዘርፉን ለማሳደግና ለማስፋፋት የሚሰራውን ሥራ እንደሚጠበቀው እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት በተሟላ ሁኔታ ወደ ተግባር ለማሸጋገር እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

**<u>የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና</u>**

**<u>መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅም</u>**

**<u>መገንባትን በተመለከተ፣</u>**

48. ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለመገንባት ድጋፍ (የቴክኒክ፣ የማቴሪያል፣ የገበያ ትስስር፣ ወዘተ) ሊያደርግ ይገባል፡፡

49. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ፡-

- የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለመገንባት በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመታት ለቆዳ፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ለኮንስትራክሽን እና በ2005 በጀት ዓመት በቆዳ፣ ለስኳር፣ ለሲሚንቶ፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ለኮንስትራክሽንና ለተሽከርካሪ ኢንዱስትሪዎች የመለዋወጫ አካላትን በራሱ ወርክሾፕ ለማምረትና በዘርፉ ለተሰማሩት ለማቅረብ በዕቅድ የያዘ ቢሆንም አለማከናወኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት በመንግስት ልዩ ትኩረት ለተሰጣቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች (ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ፣ ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች፣ ለብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች) ፈጣን እንቅስቃሴ ያላቸው 955 ዓይነት የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ኮምፖኔንቶች በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ የኢንጅነሪንግ ተቋማት እንዲመረቱ ለማድረግ እስከ 3ኛ ሩብ ዓመት እቅድ ቢይዝም 243 ዓይነት (የዕቅዱን 25 በመቶ) ብቻ መመረታቸውን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

50. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአገሪቱ ውስጥ መመረት የሚችሉ መለዋወጫዎችን በመለየት የመስራት ሥራ በተወሰኑ ኢንዱስትሪዎች የተጀመረ መሆኑን በተጨማሪም ወደ 20 የሚደርሱ ኢንዱስትሪዎችን መርጠው ከነዚህ መካከል 12ቱ መልካም ፈቃደኝነታቸውን በማሳየታቸው ለማከናወን እንዳቀዱ ቢገልፁም ስለተከናወኑ ስራዎችም ሆነ ለማከናወን ስላቀዳቸው ተግባራት ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡
51. በመውጫ ስብሰባ ወቅት የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በዘርፉ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች አስተባብረን የምናሰራው ስራ በመሆኑ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

52. ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸውን መለዋወጫ አካላት በተገቢው መልኩና በቀላሉ በአገር ውስጥ ተመርተው አለማግኘታቸው ዘርፉ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ይደርስበታል የተባለውን ግብ እንዳይመታ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ ከመንግስት እና ከግል ተቋማት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ

53. ኢንስቲትዩቱ ከብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ጋር አጋዥ ሥራዎችን ከሚሰሩ መንግስታዊ፤ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ዓለም-ዓቀፍ ተቋማት ጋር የመረጃ ልውውጥ እና የተጠናከረ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊፈራረም ይገባል፡፡

54. በኦዲቱ ወቅትና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገው ውይይትና ከተከለሱ መረጃዎች

- ኢንስቲትዩቱ ከአዲስ አበባ የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከል፣ ከፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ፣ ከብሄራዊ ስነ ልክ ኢንስቲትዩት ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረማቸውን እንዲሁም የመግባባቢ ሰነድ ባይፈራረሙም ከአለምአቀፉ የአቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ እና ከተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ጋር የመረጃ ልውውጥ እንደሚያደርጉ፣ በአገር ውስጥ በግሉ ዘርፍ ከተሰማሩ 191 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 52 ኢንዱስትሪ በመምረጥ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገላቸው ሲሆን በድርጅቶቹም ውስጥ መተባበርን በማስረፅ በጋራና በቅንጅት እንዲንቀሳቀሱ እያደረገ መሆኑ፣
- በአገሪቱ ትልቁ የኢንዱስትሪ እድገት ሞተር ከሆነውና በዘርፉ ትልቅ ኃላፊነትን ከተረከበው ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር የጠበቀ የስራ ግኑኝነት ወይም ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑን፣ በብረታ ብረት ዘርፍ አጋዥ ስራዎችን ከሚሰሩ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ለመዘርጋት በአገር ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር ኮሚቴ አዋቅሮ ችግሮችን ለመቅረፍ በ 2006 ዓ.ም እቅድ ቢይዝም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ተግባራዊ አለማድረጉን

ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. ይህን በተመለከተ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቅርቡ ከህንድ አገር የሚገኝ አቻ ኢንስቲትዩት ጋር ቁርኝት (twinning) መጀመራቸውን፣ በሌሎች ተቋማት ግንኙነቱን ለማጠናከር እየሞከሩ መሆኑን እና ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር የውጭ አገር ሥልጠና ሲኖር የሚያሳትፉ ሲሆን ከዚህ ውጭ ግን

ኮርፖሬሽኑ አቅሙ የጠነከረ ስለሆነ በራሱ ሥራዎቹን የሚሰራ በመሆኑ እገዛ እንዳላደረጉለት ገልፀዋል፡፡

56. ኢንስቲትዩቱ ከግል እና ከመንግስት ባለድርሻ አካላት ጋር በተጠናከረ መልኩ በቅንጅት አለመስራቱ በግል እና በመንግስት የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ እንዱስትሪዎች የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዳይኖር፣ ዘርፉ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚፈልገውን ድጋፍና ትብብር ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እንዳያገኝ በማድረግ የብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪውን እድገት ያጓትተዋል፡፡

## 2.2 የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማምረት እንዲችሉ እና ምርቶቹም የገበያ ድርሻን ማሳደግ እንዲችሉ በኢንስቲትዩቱ የሚሰጠው ድጋፍ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

<u>በኢንስቲትዩቱ ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጡ የቴክኒክ ድጋፎችን በተመለከተ</u>

57.ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ የምርት ጥራትና ምርታማነትን ለማሳደግ የጥራት ደረጃ ዝግጅት፣ የጥራት ፍተሻና ማረጋገጫ ድጋፎችን እንዲሁም የላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጥ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ በመሰረታዊ ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ዘርፉን ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን ሊያዘጋጅና ሊሰጥ ይገባል፡፡

58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ፡-

- በ2004 በጀት ዓመት ለ50 ምርቶች የጀረጃ ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት ቢያቅድም ለአንድ ምርት ብቻ (አልሙኒየም ዚንክ ቅብ የቤት ክዳን ቆርቆሮ) ደረጃ ተዘጋጅቶና ፀድቆ ወደ ትግበራ የገባ መሆኑ እንዲሁም ለ10 ምርቶች የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ፍተሻ አገልግሎት ለመስጠት በዕቅድ ቢያዝም ስራው ያልተከናወነ መሆኑ፣

- በ2005 በጀት ዓመት የደረጃ ዝግጅት፣ የጥራት ፍተሻና የላቦራቶሪ አገልግሎት ለመስጠት የጥራት ደረጃ ሊወጣላቸው እና ሊከለስላቸው የሚገባቸውን የምርት ዓይነቶች በመለየት፣ ለደረጃዎች ኤጀንሲ የቀረበውን የጥራት ደረጃ መግለጫ ፕሮፖዛል በመከታተል ለማስፀደቅ 25 ለሚሆኑ ኢንዱስትሪዎች በእቅድ ቢይዝም 13 ፕሮፖዛል ብቻ ያከናወነ መሆኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት 38 ደረጃ የሚወጣላቸው /የሚሻሻሉ/ ምርቶችን ለመለየትና የምርት ጥራት ደረጃ ፕሮፓዛል ለማዘጋጀት እቅድ ቢይዝም እስከ 3ኛው ሩብ ዓመት 28 ፕሮፖዛል ያዘጋጀ መሆኑ፣ እና የኢትዮጵያ ስቲል ፕሮፋይሊንግ እና ቢውልዲንግ የተባለ ድርጅት ለኤጋ ምርቶች የጥራት ፍተሻ እንዲደረግለት ጠይቆ ምላሽ ያላገኘ መሆኑን፣
- ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ብቁ ሙያተኞች በሙያ ዓይነት፣ በደረጃና በመጠን በመለየት በተለዩት የሙያ ክፍተቶች ላይ በ2006 በጀት ዓመት እስከ 3ኛው ሩብ ዓመት ለ390 ባለሙያዎች (35 በመቶ ለሴቶች) ስልጠና ለመስጠት ቢያቅድም ለ118 (30.26 በመቶ) ባለሙያዎች ብቻ ስልጠና የሰጠ ሲሆን ከነዚህ ስልጠናውን ከወሰዱት መካከል የሴቶች ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ አለመገለፁን፣
- በምርት ጥራት፣ በማሽኒንግ፣ በኳሊቲ ማኔጅመንት፣ በሚሊንግ፣ በኢ-አበላሽ {Non Distractive testing (NDT)} እና በግሪንዲንግ በ2004 ዓ.ም 20,579 ሰዓት ስልጠና ለመስጠት አቅዶ 64 ሰዓት ብቻ ሥልጠና መስጠቱን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

59. ይህንን በተመለከተ የኢንስቲትዩቱ የምርትና ዲዛይን ሃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኢንስቲትዩቱ መስፈርት የሚያስፈልጋቸውን ምርቶች እየለየ ለደረጃዎች ኤጀንሲ እንደላከ፣ ከዚህ በፊትም የአርማታ ብረት፣ የቱቦላሬ ፕሮፋይል መስፈርት እንዲወጣላቸው ማድረጉን፣ በተለያዩ ዘርፎች ከኢንዱስትሪዎች የስልጠና ፍላጎት መረጃ በመሰብሰብ ስልጠናዎችን እየሰጠ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
60. የኢንስቲትዩቱ የምርትና ዲዛይን ኃላፊ በ2004 ዓ.ም አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ስለመሆኑና የኢትዮጵያ ስቲል ፕሮፋይሊንግ እና ቢልዲንግ የተባለ ድርጅት ለኤጋ ምርቶች የጥራት ፍተሻ እንዲደረግለት መጠየቁን በተመለከተ ከመውጫ ስብሰባ በኋላ በቀረበው ማስረጃ መሰረት የኤጋ ምርቶች የጥራት ደረጃ ስለሌላቸው ደረጃ እንዲወጣለት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ለደረጃዎች ኤጀንሲ መላኩን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልፀዋል፡፡

61.በመሆኑም በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች በተከታታይ ፍተሻ ጥራታቸውን የጠበቁ ምርቶችን እንዲያመርቱ ባለመደረጉ ምርቱ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡ እንዲሁም የኢንዱስትሪዎችን የስልጠና ፍላጎት በመዳሰስ በቂ የሆነ ስልጠና አለመስጠቱ ዘርፉ በየወቅቱ ከሚመጡ ቴክኖሎጂዎች ጋር በማስተዋወቅ ሊገኝ በሚችለው እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

## ብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥ እና በውጭ አገር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ፣

62.የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ምርት የማስተዋወቅና የገበያ ጥናትና ትስስር ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም በኢንዱስትሪዎቹ የሚመረቱ ምርቶች ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥና ለውጭ ገበያ የተመረቱ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ ለመሸጥ የሚያስችል የገበያ መረጃ፣ የገበያ ፍለጋ እና መደበኛ የገበያ ትስስር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

63.በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ፡-

- በ2004 በጀት ዓመት ለ20 ኢንዱስትሪዎች ምርት የማስተዋወቅና የገበያ ትስስር ድጋፍ ለመስጠት ፋብሪካዎቹ የሚጠቀሚቸው ግብዓቶች፣ የሚያመርቷቸው ምርት ዓይነቶች እና የማምረት አቅማቸው መረጃ ከ25 ፋብሪካዎች የተሰበሰበ ቢሆንም ትስስር የመፍጠሩ ስራ ስለመከናወኑ የሚገልጽ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ መሆኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት 20 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ፕሮፋይል በማዘጋጀት ለማስተሳሰር፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የግብዓትና የገበያ ትስስር ለመፍጠር፣ እንዲሁም በግብዓትና ምርት ሊተሳሰሩ የሚችሉ ኢንዱስትሪዎችን ለማዋዋል በእቅድ ቢይዝም እስከ 3ኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ የተከናወነ ስራ አለመኖሩን፣ ኤክስፖርት የሚያደርጉ የንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪዎች በዘጠኝ ወር ውስጥ 5873.6 ሺህ የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 3884.72 ሺህ ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙ የእቅዱን 66.12 በመቶ ብቻ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ምርቶችን የማስተዋወቅና የገበያ ጥናት ትስስር ለመፍጠር በአርማታ ብረት ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች አቅም መጎልበትን አስመልክቶ ለከተማና

ኮንስትራክሽን ልማት ሚኒስቴር ደብዳቤ የፃፈ መሆኑ፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ከሀንፃ አቅራቢ ድርጅት ጋር በመሆን በጋራ ግዥ የሚፈፅሙበትን በማመቻቸት 10 ሺ ቶን ብረት መግዛት መቻላቸውን እንዲሁም የጋራ ስምምነቶችን በማድረግ አለም አቀፍ ጨረታ ላይ መሳተፍ መጀመራቸውን እንዲሁም የተለያዩ ኤግዚብሽኖች ላይ መሳተፍ እንዲችሉ መረጃዎችን መሳተፍ ይችላሉ ብለው ላመኑባቸው ድርጅቶች የሚያሳወቁ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም በናሙና የታዩ ድርጅቶች በገበያ እጦት ምክንያት ምርቶቻቸው በመጋዘኖቻቸው ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፣

ለመረዳት ተችሏል፡፡

64. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ ኢንዱስትሪዎች (አስመን ኃ.የተ.የግ.ማህበር፣ ስቲሊ አር ኤም አይ ኃ.የተ.የግ.ማህበር፣ አለም ስቲል፣ አሚዩ ኢንጂነሪንግ፣ ኬጂ ኢንጂነሪንግ፣ የኢትዮጵያ ባሌስትራ ፋብሪካ አ.ማህበር፣ ብስራት ኃ.የተ.የግ.ማህበር፣ የኢትዮጵያ ስቲል ፕሮፋይሊንግና ቢልዲንግ) ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- በዘርፉ የተጠናከረ የገበያ ጥናት ባለመኖሩ በአሁኑ ወቅት የአርማታ ብረት ምርት ገበያውን የሸፈነ ቢሆንም በዚህ ዘርፍ መንግስት ተጨማሪ ኢንቨስትመንት እየሳበ እና አዳዲስ ኢንቨስተሮች እየገቡ በመሆኑ የገበያ ፍላጎትና አቅርቦት ያለመመጣጠን ሊመጣ እንደሚችል ስጋት እንዳላቸው፣ እንዲሁም መንግስት በተማከለ ደረጃ የብረት ግዥ ከፈፀመልን በኋላ የተለያዩ መጠን ያላቸውን ብረቶች አምርተን ለገበያ አቅርበን እያለ መንግስት ከኛ ከመግዛት ይልቅ ከውጭ አገር ምርት ስለሚገዛ የገበያ እጥረት መኖሩ፣ የምርት ትስስር አለመፈጠሩ እና የመሳሰሉትን ችግሮች ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና ሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ቢያሳውቁም የተሻሻለ ነገር እንደሌለ፣ እና
- 7ቱም ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃን ከውጭ አምጥቶ፣ በየብስ አጓጉዞ ፕሮሰስ አድርጎ እንደገና ለውጭ ገበያ ማቅረቡ ከፍተኛ ወጭ ስላለውና ከዋጋ አንፃር አዋጭ ባለመሆኑ (Lack of Competitiviness) ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ ማቅረብ አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡

65. እንዲሁም የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ኃላፊዎች ስለሁኔታው በሰጡት መልስ ብዛት ያላቸው መለዋወጫዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ምርቶች በገበያ ችግር ምክንያት በስቶክ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

66.ይህንን በተመለከተ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መለዋወጫ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የገበያ ትስስር ለመፍጠር እየሰሩ ቢሆንም ችግሮቹን

አጥንተው ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባቀረቡት መሰረት ወደፊት በትብብር ሊፈታ የሚችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

67. በመሆኑም የገቢያ ጥናትና የገቢያ ትስስር ባለመኖሩ ዘርፉ ለማደግ እንቅፋት ሊፈጥርበት የሚችል መሆኑ፣ አቅርቦትና ፍላጎትን ያላማከለ የምርት መትረፍረፍ ሊያስከትል እንዲሁም መንግስት ከዘርፉ ሊሰበስብ ያቀደውን ግብርና ቀረጥ በማሳጣት የመንግስትን ገቢ ሊቀንስ እንደሚችል ይታመናል፡፡

## <u>የውድቅዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና አያያዝን በተመለከተ</u>

68.ኢንስቲትዩቱ የውድቅዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና ግብይት ሥርዓት የሚይዝበትን ሁኔታ በማጥናትና በማስፈቀድ ተግባራዊነቱን ሊከታተልና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

69. ኢንስቲትዩቱ የውዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና ግብይት ሥርዓት የሚይዝበትን ሁኔታ በማጥናትና በማስፈቀድ ተግባራዊነቱን ያልተከታተለና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ውድቅዳቂ ብረት (ስክራፕ) ከተለያዩ ድርጅቶች ሰብስቦ ለማቅለጫ ፋብሪካዎች በግብዓትነት እንዲውል የሚያከፋፈለው የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የማቅለጫ ፋብሪካዎች የውዳቂ ብረታ ብረት ፍላጎትና አቅርቦት ያልተመጣጠነ እና የመግዣ ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱን ፋብሪካዎቹ ገለጸዋል፡፡

70.ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቀደም ብሎ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች በተላከው ሰርኩላር መሰረት ብረታ ብረቶች ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የተሰጡ ሲሆን አጠቃቀምን በተመለከተ በኮርፖሬሽኑ መመሪያ መሰረት እንደ ኢንዱስትሪዎቹ አቅም እያከፋፈለ መሆኑ፣ ሆኖም የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምን ያህል ውድቅዳቂ ብረታ ብረት እንደሚፈልጉ አቅማቸውን ማወቅ፣ ፍትሃዊ ክፍፍልና በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር የኢንስቲትዩቱ የስራ ድርሻ እንደሆነና መመሪያ እንደሚያስፈልገው ሆኖም በኢንስቲትዩቱ የተሰራ ሥራ አለመኖሩን፣ በየካቲት 2006ዓ.ም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተፃፈ ደብዳቤ ውዳቂ ብረቶችን የመከታተል ኃላፊነት የመንግስት ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ በኮሚቴ ውስጥ ተካቶ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

71. የውድቅዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና አያያዝን በማጥናትና በማስፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆን ባለመደረጉ የውድቅዳቂ ብረታ ብረት አቅርቦትና ግብይት ሥርዓት እንዳይዝ፣ ፍትሃዊ ክፍፍል እንዳይኖርና ህብረተሰቡ ብረት ያለውን ዋጋና የሚሰጠውን ጥቅም እንዳያውቅ አድርጓል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

72. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በአገሪቱ ውስጥ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን ድጋፍ የመስጠትና የፕሮጀክት አፈፃፀማቸውን የመከታተል አገልግሎት እንደሚሰጥ ይታወቃል፡፡ የዚህ ክዋኔ ኦዲት ዓላማ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በዘርፉ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን የመደገፍና የፕሮጀክት አፈፃፀማቸውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር በኦዲቱ ወቅት የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን የሚገልጽ ዝርዝር ወቅታዊ መረጃ እና የፕሮጀክት ፕሮፋይል በተሟላ መልኩ ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ስለሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ለህብረተሰቡ ያላስተዋወቀና ለባለሀብቶች ያላሰራጨ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ከ2004-2007 ባዘጋጀው ስትራቴጅክ ውጤት ተኮር እቅድ ላይ በብረታ ብረት እና ኢንጅነሪነግ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለ ሀብቶች የቅድመ አዋጭነትና የአዋጭነት ጥናት በዕቅዱ መሰረት ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ በ2006 በጀት ዓመት 7 ለሚደርሱ ፕሮጀክቶች የዲዛይንና ግንባታ፣ የኮሚሽኒንግ፣ የማሽነሪ ተከላና የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ቢያቅድም እስከ 3ኛው ሩብ ዓመት ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ዘርፉን ለማሳደግ እንቅፋት የሚሆኑ ሕጎች፣ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎችን ግልፅ በሆነና በማያሻማ መልኩ በጥናት ያልለዩ መሆኑ፣
- ከውጭ ተመርተው የሚገቡ ዕቃዎች ጥራት፣ ቁመትና ውፍረት ላይ ቁጥጥር አለመደረጉ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎች ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያደረሰ መሆኑ፣
- የኤሌክትሪክ ብክነትን ለመቀነስ ተብሎ የኃይል መቆጣጠሪያ መሳሪያ (Power factor corrector) ለመግጠም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

ከሁለት ዓመት በፊት ከፋብሪካዎች ክፍያ የሰበሰበ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

- ❖ ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ጋር በሚሰሩ መንግስታዊ ድርጅቶች የመግባቢያ ሰነድ ያልተፈረመ መሆኑ፣
- ❖ ኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪውን መሰረት ለማስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ማለትም ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙና ሰፊ የገበያ ድርሻ ያላቸው፣ የግብርና ምርቶችን በግብዓትነት የሚጠቀሙ የኢንዱስትሪ መሳሪዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን የሚገነቡ ኢንዱስትሪዎችን ትኩረት ሰጥቶ እንዲስፋፉና አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙ እና ዘርፉን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ጥናትና ምርምር ስራዎች ያላከናወነ መሆኑ፣
- ❖ ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለመገንባት ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፣
- ❖ ኢንስቲትዩቱ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ተመሳሳይ አላማ ካላቸው የመንግስትና የግል ተቋማት ጋር ትብብር ለማድረግ የመግባቢያ ሰነድ ከአብዛኞቹ ጋር ያልተፈራረመ መሆኑ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ያልዘረጋ እና ቅንጅታዊ አሰራር የሌለ መሆኑ፣
- ❖ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መሰረተ ልማት እንዲያገኙ ኢንስቲትዩቱ የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ የሚረዳቸው ቢሆንም ድጋፉን ስለማግኘታቸው ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤
- ❖ ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ የምርት ጥራትና ምርታማነትን ለማሳደግ የጥራት ደረጃ ዝግጅት፣ የጥራት ፍተሻና ማረጋገጫ ድጋፎችን በእቅድ ባስቀመጠው መሰረት ያልሰጠ መሆኑ፣
- ❖ በኢንስቲትዩቱ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የፖሊሲና የህግ ድጋፍ፣ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ የግብይት ስትራቴጂ ለመንደፍ እና ተጓዳኝ ድጋፍ ለማድረግ በስትራቴጅክ እቅድ የተያዘ ቢሆንም ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

- በንዑስ ዘርፉ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች የሚያስገኙት የኤክስፖርት ገቢ ከእቅዱ አንፃር አፈፃፀሙ አነስተኛ መሆኑ፤

- ኢንስቲትዩቱ የውድቅዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና ግብይት ሥርዓት የሚይዝበትን ሁኔታ በማጥናትና በማስፈቀድ ተግባራዊነቱን ያልተከታተለና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

73. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

74. ኢንስቲትዩቱ፤ ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል፣ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን እንዲሁም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ማስፈፀም የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

- ✓ ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ዝርዝር መረጃ ማለትም-- (የኢንዱስትሪውን ስም፣ የባለቤትነት አይነት፣ የስራ አድራሻ፣ የድርጅቱን አላማ፣ የካፒታል መጠን፣ ወደ ሥራ የገባበት ዘመን፣ የተሰማራበት ዘርፍ፣ የተጠቀማቸው ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች አይነት፣ ለአገር የፈጠረው ፋይዳ ማለትም በስራ እድል፣ በአመት የማምረት አቅም፣ የሚመረተው ምርት አይነት፣ የተጠቀመው ቴክኖሎጂ፣ የሚጠቀመው ግብአትና መጠን ወዘተ) ሊይዝ ይገባል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ የዋና ዋና ግብዓቶችን የዋጋ ተመን መግለጫ (Factor cost) እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር መረጃውን ለሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ማግኘት የሚችልበትን ዘዴ በመጠቀም ለምሳሌ በመረጃ ድረገፅ (web-site) ሊያስተዋውቅ ይገባል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የመሰረተ ልማት ድጋፍ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገርና ክትትል በማድረግ ድጋፉን ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና በድጋፉ ተጠቃሚ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማለትም በየፕሮጀክት ሂደት (project phase) የሚያስገቡዋቸውን የተለያየ መጠን ያላቸው በግብአትነት የሚውሉ ቁሳቁሶች፣ ማሽነሪዎች ወዘተ ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ እና ሌሎች ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ኢንስቲትዩቱ ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተላቸው 52 ኢንዱስትሪዎች እያንዳንዳቸው ፕሮጀክታቸውን የሚገልፅ የፕሮጀክት ፕሮፋይል በኢንስቲትዩቱ ሊኖራቸው (ሊዘጋጅላቸው) ይገባል፡፡

- ➢ ኢንስቲትዩቱ በባለሃብቱ የተዘጋጀውን የአዋጭነት ጥናት ለማበልፀግና አስተያየት ለመስጠት የሚያስችሉ መስፈርቶችን አውጥቶ በመጠቀም የተሰራውን ስራ በግልፅ ሊያሳይ ይገባል፡፡

- ➢ ኢንስቲትዩቱ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የፖሊሲና የህግ ድጋፍ፣ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸትና የግብይት ስትራቴጂ በመንደፍ ተጓዳኝ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ➢ ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚያስፈልጉትን የጥሬ ዕቃዎችና የተለያዩ ግብዓቶች ለሚያስመጡ አምራቾች የውጭ ምንዛሬ ቅድሚያ እንዲያገኙ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ➢ የብድር አሰጣጥ ስርዓቱ ለውጭ ባለሃብት እና ለአገር ውስጥ ባለሃብት ተመሳሳይ የሆነ መብት (ማለትም የውጭ ባለሃብት ያገለገለ ማሽነሪ ይዞ አገር ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ ሲመጣ አሮጌው ማሽነሪ ዋጋ እንደብድር ማስያዣ ከመቆጠሩም በላይ ተጨማሪ ብድር የሚመቻችለት ሲሆን ለአገር ውስጥ ባለሃብትም ተመሳሳይ ማበረታቻ አያገኝም) እንዲያገኙ ተገቢውን ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡

- ➢ መንግስት በሚያከናውናቸው የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ዘርፈ ብዙ ግብአቶችን ማለትም (የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችን፣ የጭነትና ገልባጭ ተሽከርካሪዎችን፣ የመስክ ተሽከርካሪዎችን፣ አርማታ ብረቶችን፣ ቆርቆሮዎችን፣ ቱቦላሬዎችን፣ ትራንስፎርመር፣ የኤሌክትሪክ ሞተሮችና ገመዶች ወዘተ) የሚገዛ ሲሆን የአገር ውስጥ አምራቾችም ምርት እንዲጠቀሙ ቅድሚያ የሚሰጥ ወይም ከጨረታው የተወሰነ ድርሻ መጠን ለአገር ውስጥ አምራቾች የሚሰጥ የአሰራር ሥርዓት የሚዘረጋበትን ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋጋር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ➢ ያለቀለት ምርት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ እና ተመሳሳይ ምርት በአገር ውስጥ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ሲመረት ወይም ሲገጣጠም ለአገር ከሚሰጠው ፋይዳ (ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር ወዘተ) አንፃር ከውጭ ከሚገባው ምርት ጋር በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያደረግና የአገር ውስጥ ምርት ቅድሚያ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ሊሰራ ይገባል፡፡

- ለግብርና ግብዓቶች የተሰጠው የቀረጥ ማበረታቻ /መብት/ በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ በተሰማሩ አምራች ድርጅቶች ለሚመረቱ ትራክተሮች፣ ተቀፅላዎችና የውሃ ፓምፖች የሚካተቱበትን ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ በማጥናት ለሚመለከተው የመንግስት አካል የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- በዋራንቲ ጊዜ ለተበላሹ ወይም ቀድመው ተሟልተው ባልተላኩ ግብአቶች በምትክነት ለሚገቡ እቃዎች ጉምሩክ እንደግብአት በሁለተኛ መደብ ታሪፍ ሳይሆን እንደ መለዋወጫ እቃ ከፍተኛ ቀረጥ የሚያስከፍል ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ኤል ሲ ተከፍቶ ያልገባ ነው በማለት በቅጣት የዕቃውን ዋጋ ሶስት እጥፍ እንዲከፍል የሚያስገድድበት መመሪያ እንዲሻሻል ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር መፍትሔ የሚገኝበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ከውጭ ተመርተው የሚገቡ የንዑስ ዘርፉ የምርት ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር በማድረግ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ በማድረግ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎች ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ቁጥጥር የሚደረግበትን ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊያመቻች ይገባል፡፡
- የኤሌክትሪክ ኃይል በበቂ ሁኔታ አለመቅረብና በየጊዜው የሚታየው የኃይል መቆራረጥ የመለዋወጫ መቃጠልና የምርት መስተጓጎል ችግር እንዳይከሰት ጄኔሬተር የሚጠቀሙ መሆኑ ይህም ለተጨማሪ ወጭ የሚዳርጋቸው በመሆኑ አምራቾች ከኮርፖሬሽኑ ጋር በገቡት ውለታ እና በከፈሉት መጠን የኃይል አቅርቦት የማያገኙ በመሆኑ ችግሮቹ እንዲቀረፉ ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የኤሌክትሪክ ብክነትን ለመቀነስ ተብሎ የኃይል መቆጣጠሪያ መሳሪያ (Power factor corrector) ለመግጠም የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽኑ ከሁለት ዓመት በፊት ከፋብሪካዎች ክፍያ የሰበሰበ በመሆኑ መሳሪያው በአፋጣኝ የሚገጠምበትን ሁኔታ ኢኒስቲትዩቱ ክትትል ሊያደርግና የአምራቾቹ ችግር መቀረፉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግሮችና ክፍተቶችን ሊቀርፉና ሊሞሉ የሚችሉ ጥናቶችን ለማጥናትና ለማስጠናት በስትራቴጂክ እቅዱ እና በአመታዊ እቅዱ ለይቶ ሊሰራ ይገባል፡፡ እንዲሁም የተጠኑ ጥናቶችን በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሃብቶችን በመለየትና የማሳወቅ ስራዎችን በአግባቡ ሊያከናውን ይገባል፡፡

75. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ምርት ማምረት እንዲችሉ እና ምርቶቹም የገበያ ድርሻን ለማሳደግ በኢንስቲትዩቱ የሚሰጠው ድጋፍ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤


- የገበያ ክፍተትን በሚሞሉ እና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማፍለቅ በመንግስትና በልማታዊ ባለሀብቱ ቅንጅት ኢንቨስት እንዲደረግ ለመስራት በስትራቴጅክ እቅድ በመያዝ ሊያከናውን ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለመገንባት በዕቅድ ይዞ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በመንግስት ልዩ ትኩረት ለተሰጣቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች (ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ፣ ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች፣ ለብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች) የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ኮምፖኔንቶች በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ የኢንጅነሪንግ ተቋማት እንዲመረቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በአገራችን ትልቁ የኢንዱስትሪ እድገት ሞተር ከሆነውና ትልቅ ኃላፊነትን ከተረከበው ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር የጠበቀ የስራ ግኑኙነት በመፍጠር አንዱ ለሌላኛው አቅም ሊሆን የሚችልበትን አሰራር ሊፈጥር ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ተመሳሳይ ተግባር ከሚያከናውኑ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ተመሳሳይ አላማ ካላቸው የመንግስትና የግል ተቋማት ጋር የጠበቀ ግንኙነት (በስልጠና፣ በልምድ ልውውጥ፣ በገበያ ትስስር ወዘተ) ሊመሰርት ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረት ዘርፍ አጋዥ ስራዎችን ከሚሰሩ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር እንዲሁም በአገር ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን በመዘርጋት የዘርፉን ችግሮች በተሻለ ለመቅረፍ እንዲያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊፈራረም ይገባል፡፡
- የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ምርት የማስተዋወቅና የገበያ ጥናትና ትስስር ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም በኢንዱስትሪዎቹ የሚመረቱ ምርቶች

ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥና ለውጭ ገበያ የተመረቱ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ ለመሸጥ የሚያስችል የገበያ መረጃ፣ የገበያ ፍለጋ እና መደበኛ የገበያ ትስስር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ የውዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና ግብይት ሥርዓት የሚይዝበትን ሁኔታ በማጥናትና በማስፈቀድ እንዲሁም መመሪያ በማውጣት ተግባራዊነቱን ሊከታተልና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

76. በመጨረሻም ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የብረት ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችና ባለድርሻ አካላት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

**አባሪ 1 የኢንስቲትዩቱ ሥዕላዊ የአሰራር ስርዓት መግለጫ (System description)**



## አባሪ 2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት |
|---|
| 1. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት እንዱስትሪዎችን በተመለከተ የተሟላ ወቅታዊ መረጃ፣ የፕሮጀክት ፕሮፋይል ሊያዘጋጅ እና ለዘርፉ ስለሚሰጠው ድጋፍ ለህብረተሰቡ ሊያስተዋውቅና ለባለሀብቶች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| 2. ኢንስትትዩቱ ወደ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሚገቡ ባለሃብቶች የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት፣ የኢንቨስትመንት ጋይድላይን እና የዋጋ ተመን መግለጫ (factory cost sheet) በማደራጀት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| 3. የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ እንዱስትሪዎችን ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት፣ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 4. ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላ፣ በርክክብ ፍተሻ፣ እና የኮሚሽኒንግ የማማከር ድጋፎችን በተቀላጠፈ መልኩ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| 5. ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረት ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የተሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ድጋፎች (ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ቦታዎች፣የባንክ ብድሮች ወዘተ) ለታለመላቸው አላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| 6. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት አማራጭ የኢንቨስትመንት እድሎችን የሚያስተዋውቁ የውይይት መድረኮችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| 7. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ ተግባራዊ እና ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| 8. ኢንስቲትዩቱ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ትብብር ሊያደርግና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ሊያበረታታ ይገባል፡፡ |
| 9. ኢንስቲትዩቱ ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ጋር አጋዥ ስራዎችን ከሚሰሩ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ዓለም-ዓቀፍ ተቋማት ጋር አስፈላጊ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊዘረጋና የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ሊፈጥር ይገባል:: |
| 10. ኢንስቲትዩቱ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡ ባለሀብቶች የመሬት እና መሰረተ ልማት አገልግሎቶች (ውሃ፣ ኤሌክትሪክ፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ) እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል |


| የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት |
| --- |
| ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 11. በመንግስት የሚወጡ ፖሊሲዎችንና የአፈጻጸም ህጎችን ለባለሀብቱ አሳታፊ የምክክር መድረክ በመፍጠር፣ የሚከሰቱ ችግሮችን በጋራ ተወይይቶ በፍጥነት መፍትሄ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይገባል፡፤ |
| 12. ኢንስቲትዩቱ በሀገር ውስጥ ለማምረት ለተለዩት ገቢ ምርቶች የገበያ ፍላጎት ትንተና እና የፕሮጀክት ፕሮፋይል ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| 13. ኢንስቲትዩቱ ለማምረቻ ፋብሪካዎች የምርት መቋረጥን የሚያስወግድና ወጭ ቆጣቢ የሆነ የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| 14. ኢንስቲትዩቱ ክትትል እና ድጋፍ የሚያደርግላቸውን ኢንዱስትሪዎችና ፋብሪካዎች መረጃ በዳታ ቤዝ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| 15. ኢንስቲትዩቱ በመሰረታዊ ብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ቴክኖሎጅ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የስራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ዘርፉን ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን ሊያዘጋጅና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| 16. ኢንስትቲዩቱ የብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ምርት ጥራትና ምርታማነትን ለማሳደግ የጥራት ደረጃ ዝግጅት፣ የጥራት ፍተሻና ማረጋገጫ እንዲሁም የላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| 17. ኢንስቲትዩቱ የገበያ ክፍተትን በሚሞሉና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማፍለቅ በመንግስትና በልማታዊ ባለሀብቱ ቅንጅት ኢንቨስት እንዲደረግ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| 18. ኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪውን መሰረት ለማስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ማለትም ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙና ሰፊ የገበያ ድርሻ ያላቸው፣ የግብርና ምርቶችን በግብዓትነት የሚጠቀሙ የኢንዱስትሪ መሳሪዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን የሚገነቡ ኢንዱስትሪዎችን ትኩረት ሰጥቶ እንዲስፋፉና አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙ የተጠናከረ ድጋፍ ሊሰጥና ለባለሀብቶች ሊያስተዋውቅ ይገባል፡፡ |
| 19. ኢንስቲትዩቱ ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች የተጠናከረ የፕሮጀክት አፈፃፀም ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ፣ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 20. ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረት ዘርፍ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (Environmental Impact Assessment) እንዲደረግባቸውና በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆኑን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |

| የአዲት የመመዘኛ መስፈርት |
| --- |
| 21. ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለመገንባት ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 22. ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ለሚመረቱ ምርቶች የጥራት ፍተሻ መስፈርት (standard) ሊያወጣ ይገባል፡፡ |
| 23. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ምርት የማስተዋወቅና የገበያ ጥናትና ትስስር ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| 24. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሚመረቱ ምርቶች ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥና ለውጭ ገበያ የተመረቱ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ ለመሸጥ የሚያስችል የገበያ መረጃ፣ የገበያ ፍለጋ እና መደበኛ የገበያ ትስስር ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| 25. ግብርናውን ሊደግፉ የሚችሉ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ሊደረግና በግብርና ምርቶች ላይ እሴት የሚጨምሩ ፋብሪካዎችን በማስፋፋት የውጭ ምንዛሪ ገቢን ማሳደግ ይገባል፡፡ |
| 26. ኢንስቲትዩቱ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የፖሊሲና የህግ ድጋፍ የማመቻቸት፣ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የግብይት ስትራቴጂ መንደፍ እና ተጓዳኝ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 27. ኢንስቲትዩቱ የውዳቂ ብረታ ብረት ክምችትና ግብይት አያያዝን በማጥናትና በማስፈቀድ ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| 28. ኢንስቲትዩቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውንና አዋጭነታቸው የተረጋገጠላቸውን የብረትና ተዛማጅ ማዕድናትን የማቅለጥና የማጣራት ሥራዎችን ሊደግፉ ይገባል፡፡ |
| 29. ወደ ኢንዱስትሪው የሚገቡ ባለሀብቶች ትርፋማ በመሆን በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲኖሩ ኢንስቲትዩቱ ሊደግፋቸው ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3 በናሙና የታዩ ኢንዱስትሪዎች ዝርዝር

| INDUSTRY DESCRIPTION | PRODUCT TYPES | SUB-SECTOR | REGION | SPECIFIC LOCATION | OWNERSHIP | ESTABLISHMENT YEAR | STARTING CAPITAL | PRODUCTION CAPACITY/YEAR | OPERATIONAL/PROJECT | DIFFERENT DATA |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Alem steel plc | CIS,Galvanization service | Basic metal | Addis Ababa | Hanamariam | Ethiopian | | 20,500,000 birr | | Operational | 1 |
| Amio engineering plc | treadle pumps,Rope washer pumps,Moulds,spare parts,treshers machines,and other engineering works | Engineering | Addis Ababa | Gofa | Ethiopian | 1994 | 100,000 birr | | Operational | 1 |
| Asmen plc | Wires,nials | Basic metal | Addis Ababa | Gerji | Ethiopian | | 4,000,000,000 | | Operational | 1 |
| Stelly RMI | | | | | | | | | | |
| Biserate plc(Elfigne Bahiru CIS factory) | CIS | Basic metal | Addis Ababa | Alemgena | Ethiopian*** | | 100,000,000,000 | | Operational | 1 |
| Ethiopian leaf spring sc. | Leaf springs | Engineering | Addis Ababa | Saris | Ethiopian | 1965 | 2,000,000 birr | 396 tons | Operational | 1 |
| KG engineering plc | Block machines, Concret mixer | Engineering | Addis Ababa | Gofa | Ethiopian | 1996 | 12,000,000 birr | 600 trailers | Operational | 1 |
| Ethiopian steel profiling and building materials plc | Coloured CIS,Different profiles | Basic and Engineering | Oromia | Bishofitu | Dutch | | | | | |

## አባሪ 4 የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ 5፡ የብረታ ብረት ዘርፍ ኢንስቲትዩቱ በጥናት የለያቸው ተግዳሮቶች

- በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የሚያስፈልጋቸውን የጥሬ ዕቃና የተለያዩ ግብአቶች ለማስመጣት የውጭ ምንዛሬ ቅድሚያ የማይሰጣቸውና ከሸቀጥ አስመጪ ነጋዴ እኩል ወረፋ ጠብቀው የሚስተናገዱ በመሆኑ ዘርፉ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ባንኮቹ ከግምት ውስጥ የማያስገቡ በመሆኑ በጥሬ እቃ እጥረት ማጣት ወይም መዘግየት ምክንያት ፋብሪካዎች እንዲቆሙ እና ለምርታማነቱ መቀነስ ምክንያት እየሆነ መምጣቱ፣
- የብድር አሰጣጥ ስርዓቱ ለውጭ ባለሃብት እና ለአገር ውስጥ ባለሃብት እኩል የሚያስተናግድ አለመሆኑ ማለትም የውጭ ባለሃብት ያገለገለ ማሽነሪ ይዞ አገር ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ ሲመጣ የአሮጌው ማሽነሪ ዋጋ እንደ ማስያዥያ (collateral) ተቆጥሮ ብድር የሚመቻችለት ሲሆን ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ያሉትን ማሽነሪዎችና መለዋወጫዎች ለብድር ዋስትና ማስያዥያ የማይያዝላቸው መሆኑ፣
- መንግስት በሚያከናውናቸው የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ዘርፈ ብዙ ግብአቶችን (የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችን፣ የጭነትና ገልባጭ ተሽከርካሪዎችን፣ የመስክ ተሽከርካሪዎችን፣ አርማታ ብረቶችን፣ ቆርቆሮዎችን፣ ቱቦላሬዎችን፣ ትራንስፎርመር፣ የኤሌክትሪክ ሞተሮችና ገመዶች ወዘተ) የሚገዛ ሲሆን የአገር ውስጥ አምራቾች እንዲጠቀሙ ቅድሚያ የሚሰጥ ወይም ከጨረታው የተወሰነ ድርሻ መጠን ለአገር ውስጥ አምራቾች የሚሰጥ ስርዓትና መመሪያ ባለመኖሩ የሚወጡ ጨረታዎች በማደግ ላይ ያለውን የሀገር ውስጥ አምራች አቅም ያላገናዘበ የጨረታ መስፈርት መኖሩ ለምሳሌ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው ግዥ በአጭር የማስረከቢያ ጊዜና የጥቅል አቅርቦት በማስቀመጥ የሀገር ውስጥ አምራች የማግለል ሂደት የሚታይ መሆኑ፣
- ያለቀለት ምርት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ እና ተመሳሳይ ምርት በአገር ውስጥ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ሲመረት ወይም ሲገጣጠም ለአገር ከሚሰጠው ፋይዳ (ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር ወዘተ ) አንፃር ከውጭ ከሚገባው ምርት ጋር በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚደረግ ከለላ የሌለ መሆኑ፣ለምሳሌ ከውጭ በሚገባ ምርት ላይ ከፍተኛ የታክስ ጫና በመፍጠር የአገር ውስጥ አምራቾችን ማበረታታትና ቅድሚያ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ያልተደረገ መሆኑ፣
- ከውጭ የሚገባ ጥሬ እቃና የተሽከርካሪ አካላት በሀገር ውስጥ ለሚገጣጠሙ ተሽከርካሪ መስሪያ ግብአት ላይ ሲውልና በመለዋወጫነት ስም በቀጥታ ለሽያጭ ሲውል የተለየ

ታሪፍ ያልተቀመጠለት መሆኑ፣ ማለትም ለማኑፋክቸሪንግ ተግባር ሲውል የተደረገለት የተለየ የታክስ ከለላ (ለምሳሌ ሁለተኛ የታሪፍ ምደባ) ተጠቃሚ የማይሆን መሆኑ፣

- ምርቱ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥሞ ያለቀለት የኮንስትራክሽን ምርቶች፣ የቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎች (እንደ ዶዘር፣ ኤክስካቫተር፣ ግሬደር፣ ዊል ሎደር፣ ክሬይን ወዘተ) ወደ አገር ሲገቡ የሚጣልባቸው ቀረጥ የለም፡፡ነገር ግን ምርታቸው ያላለቀ ብትን አካላትን አስመጥተው አገር ውስጥ በብረትና ኢንጂነሪንግ የሥራ ዘርፍ በተሰማሩ ድርጅቶች የሚገጣጠሙና የተተኩ ተመሳሳይ ምርቶችን (substituted product) ግብአት የሚሆኑ ጥሬ እቃዎች የሆኑ ተሽከርካሪ አካላቶች በአገር ውስጥ ለመገጣጠም እንደሚመጡ እየታወቀ በቀጥታ ለሽያጭ እንደሚውሉ መለዋወጫዎች የሚቀረጡ መሆኑ፣
- ለተሽከርካሪ፣ ለማሽነሪ፣ ለግብርና መሳሪያዎችና ትራክተሮች ወዘተ የሚውሉ ጥሬ እቃዎች እና የምርት ሂደታቸው ተጠናቆ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች በተመሳሳይ ታሪፍ የሚቀረጡ መሆናቸው፤ ይህም የምርት ሂደታቸውን በአገር ውስጥ ለማጠናቀቅ (ለመገጣጠም) ተጨማሪ ወጭ የሚጠብቃቸው በመሆኑ ከውጭ ምርታቸው ተጠናቆ ከሚገቡ ምርቶች ጋር እኩል በዋጋ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደረጋቸው መሆኑ፣
- የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሁለተኛ መደብ የታክስ ከለላ ተጠቃሚ ለመሆን ከውጭ የገባ ጥሬ ዕቃ በአገር ውስጥ ምርት ሂደት (Value addition) 30 በመቶና ከዚያ በላይ መሆን ያለበት ሲሆን በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሐምሌ 2005 ዓ.ም ጀምሮ ይጠቀሙበት የነበረው የስሌት ቀመር በአዲስ ቀመር በመለወጡ ማለትም አብዛኛው ከ30 ከመቶ ለመሆን የሚጨመሩ ዋጋዎች (እሴት) አዲሱ ቀመር እንዳይካተቱ፡ በማድረጉ በአገር ውስጥ የሚኖረው የተጨማሪ እሴት (Value addition) 30 በመቶ ለማድረስ አዳጋች በማድረጉ በበፊቱ ስሌት ያገኙት የነበረው የታክስ ከለላ (የሁለተኛ መደብ ተጠቃሚ) እንዳያገኙ ያደረጋቸው መሆኑ፣
- የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች፣ የግብርና ቴክኖሎጂ ማሳሪያዎች፣ ትራክተሮች፣ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች በጥሬ እቃ ለፋብሪካ ምርት ግብአትነት ሲገቡ ታክስ የሚከፍሉት በግዥ ሰነድ ላይ ባለው ሳይሆን ከላይ የተጠቀሱት ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ተጠናቀው (ምርታቸው አልቆ) ሲገቡ ባላቸው የተመዘገበ የግዥ ዋጋ ቀድሞ የገባበትን ከፍተኛ ዋጋ ከጉምሩክ ኮምፒውተር የዋጋ ዝርዝር በመውሰድ በአንድ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ በመሆኑ በሁለተኛ መደብ ታሪፍ የተፈጠረውን ማበረታች የሚቀንሰው መሆኑ፣

- ከላይ የተጠቀሱት ምርቶች ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ በመጀመሪያ በተመሳሳይ እቃ ተጠናቅቆ ከሚገባው ዕቃ (ተሽከርካሪ) ከሚከፈለው እኩል ኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት ሲሆን፤ በአገር ውስጥ ለማምረት በጨመረው ተጨማሪ እሴት (value addition) ላይ ተጨማሪ በሚከፍለው ኤክሳይዝ ታክስ አስመጪው ከከፈለው የበለጠ የሚከፍል መሆኑ ማለትም በመጀመሪያ እቃው ሲገባ የተከፈለው ታክስ እንደማምረቻ ወጪ ተቆጥሮ በድጋሚ ታክስ ይሰላበታል፡፡ ይህም በተደራራቢ ታክስ (በታክስ ላይ ታክስ) እንዲከፈልበት ያደረገ መሆኑ፣
- ለአገር ውስጥ በአነስተኛ ተቋማት ሊሰራ የሚችልን ስራ ለውጭ ባለሃብት ክፍት በማድረጉ የአገር ውስጥ ባለሃብቱን የሚያፈናቅል አካሄድ መኖሩ፣
- ባለሀብቱ የሚጠበቅበትን ፎርማሊቲ አሟልቶ የመሬት አቅርቦት ሲጠይቅ መሬቱን በሚያስተዳድሩ አካላት ፈጣን ምላሽ አለማግኘት